**ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ የጋራ አቀራረብ**

ከልማት፣ ከሰብአዊነት ወይም ከሰላም ማስከበር *ሥራ* ጋር የተያያዘ ነው።

**ክፍል 1: የጋራ ራዕይ ለተግባር**

*የ2030 የዘላቂ ልማት እና የዘላቂ ልማት ግቦች አጀንዳ (SDGs[1]*) መንግሥታትን፣ የግሉ ሴክተርን፣ የሲቪል ማኅበረሰብን፣ የጋራ ድርጅቶችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ድህነትን፣ ግጭትን፣ የአየር ንብረት ለውጥን እና የተፈጥሮ አደጋዎችን በጋራ ለመቅረፍ እንዲሠሩ ለማገዝ የበለጠ ፍትሃዊ እና መጪው ቀጣይነት ያለው የወደፊት ሁኔታን ለማዘጋጀት የሚያስችል ማዕቀፍ አዘጋጅቷል።

*የሰብአዊነት፣ ልማት እና ሰላም ማስከበር (HDP[2]) ሥራዎች* ለተቸገሩ ሃገራት እና ሕዝቦች አጋርነት፣ እገዛ፣ ድጋፍ እና ጥበቃ ማድረግን *ማዕከል ያደረገ ነው። ነገር ግን እነዚህ የሰብአዊ፣ የልማት እና የሰላም ማስከበር ሥራዎች፣ በሰብአዊ፣ በልማት፣ እና በሰላም አስከባሪ ድርጅቶች ወይም አካባቢ ውስጥ ወይም አብረው የሚሠሩ ግለሰቦች በሚያደርሱት ወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ (SEAH[2]) ሳቢያ ተሸርሽረዋል።*

ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት የሌለው *ሥ*ልጣንን ያለአግባብ መጠቀም እና የእምነትን መጣስ ነው። የአቅም/የኃይል አለመመጣጠን ላይ መሠረቱን ያደረገ ሆኖ፣ አብዛኛውን ጊዜ ከእኩልነት ፣ በተለይም የሥርዓት-ፆታ እኩልነት ጋር የተቆራኘ ነው። ሴቶች እና ልጃገረዶች አብዛኛውን ጊዜ የዚህ ጉዳት ሰለባ ናቸው። እንዲሁም ወንድ ልጆች፣ አዋቂ ወንዶች እና ሌሎችም በአንዳንድ ሁኔታዎች እና በተለያዩ ምክንያቶች አቅም/ ኃይል (power) ላይኖራቸው ወይም በተለየ የተገለሉ ከሆኑ ጥቃት ሊደርስባቸው ይችላል።

በሰብአዊነት፣ በልማት እና በሰላም ማስከበር *ሥራዎች* የሚሠሩ ሁሉም፣ ከ*ሥራቸው* ጋራ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ድጋፍን፣ ጥበቃን እና ኢንቨስትመንትን በማቅረብ ረገድ በሚጫወቱት ሚና የተነሳ *ሥ*ልጣናቸውን ያላግባብ መጠቀምን ጨምሮ ወሲባዊ ብዝበዛን፣ ጥቃትን ወይም ወሲባዊ ትንኮሳን በሌሎች ላይ ሊፈጽሙ የሚችሉበትን አደጋ በንቃት መቆጣጠር አለባቸው።  እንደ የአየር ንብረት ለውጥ፣ አለመረጋጋት እና ግጭት ባሉ ምክንያቶች የወሲብ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ የመከሰት ዕድል ተባብሷል ይህም የሰብአዊ፣ የልማት እና የሰላም ማስከበር እገዛ ፍላጎት እንዲጨምር ሆኗል።

በሰብአዊነት፣ በልማት እና በሰላም ማስከበር *ሥራዎች* ውስጥ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ድርጊትን "በተግባር ላይ ዜሮ-መቻቻል" ያለመታገስ አካሄድ ለማድረግ እንቅስቃሴ ተደርጓል።  ይህ ማለት ሰዎችን እና ሰራተኞችን ከጥቃት እንዲሁም ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን ለመከላከል ሁሉንም ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ፤ ስጋቶች የሚነሱባቸውን/የሚነገሩባቸውን መንገዶች መፍጠር ወይም ማጠናከር፣ እንዲሁም ጥቃት ለደረሰባቸው መብት፣ ክብር እና ፍላጎቶች ቅድሚያ በሚሰጥ መልኩ ለስጋቶች እና ጉዳዮች በትጋት እና ጠንከር ባለ ሁኔታ ምላሽ መስጠት ማለት ነው።[2]

በተግባር ላይ የዜሮ መቻቻል (Zero Tolerance) አካሄድን ተግባራዊ ለማድረግ ፖሊሲዎች፣ ቁርጠኝነት እና ደረጃዎች ተዘጋጅተው የተግባራዊነቱ አካል ተደርገዋል። ነገር ግን በሰብአዊነት፣ በልማት እና በሰላም ማስከበር *ሥራዎች* ውስጥ አልተካተቱም ወይም በቋሚነት አይተገበሩም። ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ የጋራ አካሄድ (CAPSEAH) ለመጀመሪያ ጊዜ ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ (PSEAH)፣ ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ(SEAH) ዙሪያ የተወሰዱ የእርምጃ ልምምዶችን፣ ፖሊሲዎች እና ደረጃዎችን በአንድ ላይ በማሰባሰብ በሰብአዊነት፣ ልማት እና ሰላም የማስከበር *ሥራዎች* ውስጥ የሚሠሩ ሁሉም ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን የመከላከል *ሥራዎቻቸው* ውስጥ እንደመመሪያ ማፅደቅ እና መጠቀም እንዲችሉ ያስችላል። ከሰብአዊነት፣ ከልማት እና ከሰላም ማስከበር *ሥራ* ውጪ ሌሎችም ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ዕድል አለ።

ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ የጋራ አካሄድ ዓላማው የመከላከል ጥረትን፣ የተሻለ ተጠያቂነት፣ የመከላከል እና የተሻለ ምላሽ እና ድጋፍ ለተጎጂዎች/ከጥቃት ተራፊዎች በተናበበ መልኩ እንዲሆን ግፊት ማድረግ ነው። የምዕተ ዓመቱን የሰላም፣ ብልጽግና፣ ድህነትን ቅነሳን እና ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማስፈን ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ፣ አገራዊ እና አካባቢያዊ ጥረቶችን መደገፍ ያስፈልጋል።

ከወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ፣ የጋራ አቀራረብ አራት ክፍሎች አሉት፡- የጋራ መርሆች ዕይታ፣ ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ (PSEAH) *ሥራን* ከ*ሥ*ር ለመደገፍ የተለመዱ መርሆዎች፣ አነስተኛ የሚመከር እርምጃዎች፣ የተለያዩ ዓይነት ተዋናዮች እንዴት ድርጊቱን በተግባር ላይ ማዋል እንደሚችሉ

መመሪያ ናቸው። ሙሉው ፅትም እዚህ ድረ ገጽ ላይ ይገኛል። [capseah.safeguardingsupporthub.org] ይህ ረቂቅ እንዴት እንደተዘጋጀ እና እርስዎ በምክክር ሂደቱ ውስጥ እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ መረጃ ጋር ይገኛል።

### *ክፍል 2: ከወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ የተለመዱ መርሆች*

እነዚህ መርሆዎች በሰብአዊነት፣ በልማት ወይም በሰላም ማስከበር ሥራ ላይ የተሰማሩ ሁሉም ሰዎች እና ድርጅቶች ሥራዎችን እና ሥነ ምግባር ማጠናከር እና መምራት አለባቸው። እንዲሁም ሥራቸውን ከ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳ ጋር የተገናኘ አድርገው ቢመለከቱም ባይመለከቱትም ከሰብአዊ፣ ልማት እና ሰላም ማስከበር ዘርፎች ያለፈ ለሌሎችም አግባብነት ሊኖራቸው ይችላል።

1. **ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መፈጸም በጥብቅ የተከለከለ ነው።** ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ከፍተኛ የሥነ ምግባር ጉድለት ሊባል የሚቻል፤ የሥራ ውልን ለማቋረጥም ምክንያት ሊሆን የሚችል እንዲሁም በወንጀል፣ በሲቪል ወይም በወታደራዊ ሕግ ሊያስከስስ ይችላል። መሰል ድርጊቶች ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም እና የሰብአዊነት፣ የልማት እና የሰላም ማስከበር ጥረቶች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያደርሱ እንዲሁም ተዓማኒም እንዳይሆኑ የሚያደርጉ ናቸው። በተለየም፦
   - ሀ. **ሌሎችን አዋራጅ፣ ስብዕናን የሚነኩ ወይም ጨቋኝ ባህሪያትን ጨምሮ ገንዘብን፣ የሥራ ቅጥርን ፣ ቁሳቁስን፣ ወይም አገልግሎቶችን ፣ በወሲብ መለወጥ በጥብቅ የተከለከለ ነው።** ይኸም የሰብአዊ፣ የልማት እና ሰላም የማስከበር ተግባር ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች ድጋፍ ሊያደርጉላቸው የመጡትን ሕዝቦች ወይም ማኅበረሰቦች የሚገባውን ማንኛውንም እርዳታ ወይም ጥበቃ በወሲብ መለወጥን ይጨምራል።
   - ለ. **የሰብአዊ፣ የልማት እና ሰላም የማስከበር ተግባር ላይ በተሰማሩ ሰዎች መካከል እና የሰብአዊ፣ የልማት እና ሰላም የማስከበር ድጋፍ በሚደርጉላቸው ሰዎች ወይም ማኅበረሰቦች ወይም አብረዋቸው ከሚሠሩ ሰዎች ጋር ተገቢ ያልሆነ ሥልጣንን ወይም ደረጃን መጠቀምን ወይም ማንኛውንም ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀምን ወይም የኃይል አለመመጣጠን ጨምሮ ማንኛውም *ፆታዊ ግንኙነት* በጥብቅ የተከለከለ ነው።**
   - ሐ. **በሰብአዊ፣ በልማት እና በሰላም ማስከበር *ሥራ* ላይ በተሰማሩ ሠራተኞች እና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወይም ዕድሜያቸው ከ18 አመት በታች ከሆኑ ህጻናት መከከል የአብዛኛው በአካባቢው የተስማሙበት ዕድሜ ወይም የእድሜ ክልል ምንም ይሁን ምን የወሲብ ድርጊት መፈጸም በጥብቅ የተከለከለ ነው።** ስለ ልጅ ዕድሜ በተመለከተ የተሳሳተ ግምት መከላከያ አይሆንም።
2. **እርምጃ አለመውሰድን አለመታገስ ወይም ዜሮ-መቻቻል:** ይህም ማለት ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ለወሲባዊ ትንኮሳ ድርጊቶች ዜሮ መቻቻል፣ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን አለመከላከልን፣ ሪፖርት አለማድረግን ወይም ምላሽ ለመስጠት አለመንቀሳቀስን/ያለመተግበርን አለመታገስ እንዲሁም ከጥቃት-ተራፊዎች ወይም መረጃ አቀባዩች ላይ የሚደረገውን የበቀል እርምጃ በፍጹም አለመታገስ ማለት ነው። የወሲብ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጉዳዮች ምንም ሪፖርት አይደረጉም ማለት አይደለም። ሪፖርት ማድረግ ይበረታታል እንጂ ቅጣት አያመጣም።
3. **ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ ከጥቃት-ተራፊዎችን ያማከሉ መሆን አለባቸው።** በሰብአዊ፣ በልማት እና በሰላም ማስከበር ሥራዎች የተሰማሩ መንግሥታት፣ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ከወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃን በሚነድፉበት እና ከሠራተኞቻቸው ጋር የተያያዙ የወሲብ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጉዳዮች ላይ ምላሽ ሲሰጡ፣ ከጥቃት የተረፉትን ማዳመጣቸውን እንዲሁም ለመብታቸው፣ ለደህንነታቸው፣ ለፍላጎታቸው፣ ለሁለንተናቸው እና ለክብራቸው ቅድሚያ መሰጠቱን ማረጋገጥ አለባቸው።
4. ***ኃላፊነት* የሚሰማዎ እና ተጠያቂ ይሁኑ።** በሰብአዊ፣ በልማት እና በሰላም ማስከበር ሥራዎች የተሰማሩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች በማንኛውም ጊዜ በታማኝነት የሚሠሩ፣ እንዲሁም ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን የሚከላከል፣ ሪፖርት ለማድረግ እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አካባቢን የመፍጠር እና የመጠበቅ ኃላፊነት ሊወስዱ ይገባል። አስተዳዳሪዎች እና መሪዎች ይህንን አካባቢ የመንከባከብ ባህልን እና ሥርዓቶችን የማስተዋወቅ ልዩ ኃላፊነት አለባቸው። ኤጀንሲዎች፣ ድርጅቶች እና መንግሥታት ከወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ/የመከላከል ሥርዓቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ የተደራጁ እና የተነደፉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። የወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ስጋትን ለመለየት እና ለመቀነስ፣ ድርጊቱን ፈፅመዋል የተባሉ ሠራተኞቻቸው በሕግ እንዲጠየቁ፣ በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸውን እንዲሁም በጥቃቱ ሳቢያ የተወለዱ ልጆች ካሉ ፍትሕ እና ድጋፍ እንዲያገኙ ማገዝ አለባቸው።
5. **ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥርጣሬዎች እና ሪፖርቶች እንደደረሱ ወዲያውኑ እርምጃ ይውሰዱ።** ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ዘገባዎች፣ ስጋቶች ወይም ጥርጣሬዎች ጠንካራ እና

ከባድ እርምጃ ያስፈልጋቸዋል። በሰብአዊ፣ በልማት እና በሰላም ማስከበር ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ከሥራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴዎችን ማወቅ እና የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥርጣሬዎችን እና ሪፖርቶችን በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ አለበት። በተመሳሳይ ድርጅት ውስጥም ሆነ በሌላ ሠራተኛ ላይ ያሉ ስጋቶች ወይም ጥርጣሬዎች ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

6. **ምስጢራዊነትን ያክብሩ እና ከበቀል ይቆጠቡ።** በውንጀላው ውስጥ የተሳተፉ ሁሉም ምስጢራዊነታቸው እና ክብራቸው ሊጠበቅላቸው እንዲሁም ከበቀል እርምጃ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል። ይህ ከጥቃት የተረፉትን፣ ቅሬታ አቅራቢዎች፣ ምስክሮች እና መረጃ አቀባዩችን ያጠቃልላል።

## *ክፍል 3 ቢያንስ መደረግ ያለባቸው የሚመከሩ እርምጃዎች*

በሰብአዊነት፣ በልማት እና በሰላም ማስከበር ላይ የሚሰሩ ሁሉም ሰዎች እና ድርጅቶች ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ የተቻላቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ በክፍል 2 ውስጥ ከወሲባዊ ብዝበዛ ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ የጋራ መርሆዎችን እና እነዚህ እርምጃዎችን እንዲተገብሩ ያሳስባል። የተለያዩ ይዘት እና መጠን ያለቸው ድርጅቶች ከሥራቸው ጋር በተመጣጠነ እና ከሥራቸው ጋር በጣም በተዛመደ መልኩ ሊተገበሩት ይችላሉ።

1. ***መመዘኛዎች፡- የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ መመዘኛዎችን ፣ያሳውቁ እና ተፈጻሚ ያድርጉ።***

*ሀ.* ከእነዚህ የጋራ መርሆች እና ድርጊቶች ጋር የሚስማማ ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ ፖሊሲ/ስትራቴጂ ይውሰዱ እንዲሁም ይተግብሩ።

*ለ.* ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ፣ መርሆዎች በሥነ ምግባር ደንቦች ውስጥ መካተታቸውን ያረጋግጡ። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሥነ ምግባር ደንብ ያዘጋጁ።

*ሐ.* ሁሉም ሠራተኞች፣ በጎ ፈቃደኞች እና አጋሮች ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ ፖሊሲ/ስትራቴጂ እና የሥነ ምግባር ደንብ በሚገባ መገንዘባቸውን ያረጋግጡ። ይህንን ለሠራተኞች የግዴታ የማስተዋወቅ እና መደበኛ የክለሳ ስልጠና በመስጠት፣ በውሎች፣ የሥራ ኃላፊነቶች ዝርዝር እና የትብብር ስምምነቶችን ውስጥ በጽሑፍ ማካተትን ጨምሮ፣ ከአጋሮችን የሚጠበቀውን ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ አፈጻጸም አቅም መገምገም፣ እና በአፈጻጸም ክለሳዎች እና ግምገማዎች ላይ ስለመርሁ ተገዢነት ውይይት በማድረግ ይቻላል።

2. ***አመራር: አመራሮች በወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ላይ እርምጃ አለመውሰድን እንደማይታገስ የሚያስገነዝብ እና ተጠያቂነት የሚያሰፍን ድርጅታዊ የአሠራር ባህል መዘርጋት አለባቸው።***

*ሀ.* መሪዎች ለሠራተኞች እና ለአቻዎቻቸው ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃን አስፈላጊነት በመደበኛነት በማጉላት፣እንዲሁም ሠራተኞች እና ማኅበረሰቦች ስጋቶቻቸውን በነጻነት ማንሳት እንደሚችሉ እንዲሰማቸው የሚያደርግ አካታች፣ እና የመከባበር የሥራ ባህል እና አካባቢን በማጎልበት ቁርጠኝነት በግልፅ ማሳየት አለባቸው።

*ለ.* መሪዎች በዋናው ሥራ እና በተወሰኑ የሥራ ክፍሎች (ፕሮጀክቶች ወዘተ) ውስጥ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ፖሊሲዎችን እና አፈጻጸሞችን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊው የሰው፣ የቴክኒክ እና የፋይናንስ ምንጮች የተደገፉ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና አፈጻጸማቸውን እና ተፅዕኗቸውን መቆጣጠር አለባቸው።

*ሐ.* መሪዎች፣ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ፖሊሲዎችን እና አፈጻጸሞችን እንዲያቀናጁ፣ እንዲተግበሩ እንዲሁም አፈጻጸሙን ለእነርሱ እና ለሌሎች የውስጥ እና የውጭ ባለድርሻ አካላት ሪፖርት የሚያደርጉ ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ ቀንደኛ ደጋፊዎችን/ጠበቆች ወይም የትኩረት ማዕከሎችን መለየት፣ ማሰልጠን እና ድጋፍ ማድረግ አለባቸው።

*መ.* ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ ልዩ ኃላፊነቶችን ከፍተኛ አመራሮችን ጨምሮ በተዛማጅ የሥራ ኃላፊነቶች ዝርዝር ውስጥ እና የአፈጻጸም ግምገማዎች ውስጥ ያካትቱ።

3. ***ግንኙነት/ ተግባቦት ጉዳት ከደረሰባቸው ማኅበረሰቦች እና አጋሮች ጋር ይማከሩ፣ ያሳውቁ እንዲሁም ይቀናጁ።***

*ሀ.* የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ለወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ አፈጻጸሞችን፣ ፕሮጀክቶችን/ፕሮግራሞችን እና የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴዎችን ሲነድፉ ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ በጣም ተጋላጭ የሚያደርጋቸውን ሁኔታ ከአካባቢው ሰዎች እና ከተቻለ ከጥቃት ተራፊዎች ጋር ይምከሩ፣ያዳምጡ፣ ዕውቀታቸውንም ይጠቀሙ።

ለ. ከወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ መረጃን፣ እንዲሁም ከሲቪል ማኅበረሰብ፣ ከሴቶች እና የሰብአዊ መብት ቡድኖች፣ ብሔራዊ የሰብአዊ መብት ተሚጋች ተቋማትን ማሳተፍ፣ ከሰብአዊ፣ ልማት እና ሰላም ማስከበር ፕሮግራሞች እና ኦፕሬሽኖች ጋር ግንኙነት ያላቸው የአካባቢ ማኅበረሰቦችን፣ የጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎች እና ሌሎች ምን ምን የሥነ ምግባር ባህሪ ደረጃዎችን መጠበቅ እንዳለባቸው፣ እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው፣ ሪፖርት ካደረጉ ምን ሊፈጥር እንደሚችል፣ መብቶቻቸው እና ለእነሱ ምን ዓይነት የድጋፍ አገልግሎት እንዳለ ማሳወቅ። የአካባቢውን ሁኔታ፣ ባህሎች ባገናዘበ እና ለሁሉም ተደራሽ በሆነ መንገድ ያድርጉት።

ሐ. በተቻለ መጠን ሥራ ላይ ያሉ መዋቅሮች ላይ በመገንባት ጥቃት ለደረሰባቸው ሰዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ፣ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት፣ ከአቻዎች እና አጋሮች ጋር በመተባበር ፣ ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ አፈጻጸሞችን ውጤታማ ለማድረግ፣ ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ ቡድኖች/መረቦች እና የማስተባበር ሥራዎች ውስጥ ይሳተፉ።

**4. መከላከል፡- በሁሉም እንቅስቃሴዎች ላይ ወሲባዊ ብዝበዛን፣ ጥቃትን እና ወሲባዊ ትንኮሳን ለመከላከል ስጋትን ይገምግሙ እና እርምጃ ይውሰዱ።**

ሀ. ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጥበቃ የተወሰዱ እርምጃዎችን (የወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ስጋት ግምገማ፣ አያያዝ፣ ሪፖርት አደራረግ እና የመለየት እርምጃዎች) በተልዕኮዎች፣ በቢሮዎች፣ በፕሮጀክቶች እና በሌሎች ተግባራት አቀራረጽ እና አተገባበር ውስጥ መካተት።

ለ. የአካባቢያዊ ሁኔታን እና ጉዳት የደረሰባቸውን ቡድኖችን ልዩ ተጋላጭነት እና ፍላጎቶች መረዳት ላይ በመመሥረት የወሲብ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና የወሲባዊ ትንኮሳ ስጋቶችን ይገምግሙ። ተጠቂዎች/ ከጥቃት የተረፉት፣ ጉዳት የደረሰባቸው ማኅበረሰቦች እና ሌሎች ከፕሮግራሞች ጋር የሚገናኙ ሰዎች የሚያጋጥሟቸውን የወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ስጋቶች እንዲያወጡት እንዲሁም የመከላከል እና የአደጋ መከላከያ ዘዴዎችን በመንደፍ ሂደት ድምጽ እንዲኖራቸው አሳታፊ ዘዴዎችን ይጠቀሙ።

ሐ. የወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ፣ በተለዩ አውዶች ውስጥ እንዲከሰት የሚያስችሉ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እና ሌሎች የኃይል/የሥልጣን አለመመጣጠንን ለመፍታት ሰፊ ጥረቶችን በሚገባ ይረዱ እና ይደግፉ።

መ. የወሲብ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ የወንጀለኞች ቅጥርን ለመከላከል አግባብነት ያላቸውን የማጣራት ዘዴዎችን እና የምልመላ ሂደቶችን ይጠቀሙ።

**5. ምላሽ፡- ሪፖርት ማድረግን ያበረታቱ፣ እና ጥሰት ሲደርስ ራስዎን ተጠያቂ ያድርጉ።**

ሀ. ቅሬታዎችን ለመቀበል እና ከሠራተኞች እና ከሥራ ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ለመለየት ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተደራሽ የሆኑ ዘዴዎችን ይዘርጉ፣ ያስተዋወቁ እና ተግባራዊነታቸውን ይፈትሹ። እንዲጠቀሙባቸውም ያበረታቱ። ዘዴዎቹ አስተማማኝ እና ተግባራዊ መሆናቸውን ለመፈተሽ ግብረ መልስ እና ሌሎች ማስረጃዎችን ይፈልጉ።

ለ. ሠራተኞቻቸው ወሲባዊ ብዝበዛን፣ ጥቃትን እና ትንኮሳን እንዴት መለየት እንደሚለዩ እና ሪፖርት ከደረሳቸው ወይም ድርጊቱ መፈጸሙን ካወቁ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያውቁ መመሪያን ያዘጋጁ እና ይተግብሩ።

ሐ. የጥቃት ጉዳዮችን ወቅታዊ፣ ፍትሃዊ፣ ሚስጥራዊ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ የደረሰባቸውን እንግልት ግምት ውስጥ ያስገባ፣ ከጥቃት የተረፉ ሰዎችን ክብር፣ ፍላጎቶች እና መብቶችን ያማከለ ሁኔታ ምላሽ መስጠት እና መመርመር።

መ. ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና የወሲባዊ ትንኮሳ ጥቃት ከተከሰተ ወይም ስጋቶችን ሪፖርት ባደረጉ ወይም በምርመራ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ በሆኑ ሰዎች ላይ የበቀል እርምጃ ከተወሰደ ወቅታዊ እና ተገቢ የሆነ የዲሲፕሊን እርምጃ ይውሰዱ።

ሠ. የጥቃት ጉዳይ የወንጀል ድርጊት ነው የሚል ትርጉም ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ፣ ከጥቃት የተረፉት (ወይም ልጆች፣ ወላጆቻቸው/ተንከባካቢዎች/አሳዳጊዎች/የቅርብ ሰው) ፈቃድ እና ይህን ለማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ በሆነ ጊዜ ተገቢው ሥልጣን ላለው ወይም የህግ አስከባሪ አካል ያመልክቱ።

**6. ክትትል፡- መረጃን ለመማር፣ ለማሻሻልና አፈጻጸምን ለመከታተል ይጠቀሙ**

ሀ. ከተበላሹ ነገሮች ጨምሮ ከተሞክሮ ይማሩ።

ለ. አፈጻጸሞችን ለማጠናከር እና ለማቀናጀት ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መከላከል ተሞክሮ የተማሩትን እና ልምምዶን ያካፍሉ።

ሐ. ከወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መከላከል ያመጣውን ተፅዕኖ ለመከታተል እና ለመገምገም የሚያስችል መረጃን ይሰብስቡ (ለምሳሌ በወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና በመዝገብ ያሉ ወሲባዊ ትንኮሳ ጉዳዮች ቁጥር እና ውጤቶች፣ ግብረ መልስ፣ የዳሰሳ ጥናቶች) ይጠቀሙ።

መ. በወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ዙሪያ ያለ መረጃን ሚስጥራዊነትን በጠበቀ መልኩ ማተም እና ማጋራት፤ እንዲሁም ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መከላከል ላይ ዓለም አቀፍ ማስረጃ ማዕከልን ለማጠናከር እና ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን ለማስፈን መሆን ይኖርበታል።

[1] የዘላቂ ልማት እና የዘላቂ ልማት ግቦች አጀንዳ

[2] የቃላት፣ ምህጻረ ቃላትን እና ትርጓሜዎች የግርጌ ማስታወሻን ላይ ይመልከቱ።